# “ኀብረ ሐመልሚል”



*የአቶ መላኩ አሰፋ የልጅነት ዘመን*

*“የአረንጓዴ፣የቢጫ፣ የቀይ፣ የነጭና የጥቁር ነጠብጣብ፣ የብዙ አይነት ቀለማት ህብር፣ በማይዝግ በብር ሰሌዳ ላይ በባለሙያ የተሰሩ የወርቅ፡ ያልማዝና የዕንቁ ፈርጦች እና ጉብጉባቶች”*

# የአቶ መላኩ አሰፋ አጭር የሕይወት ታሪክ

ከቀሲስ አስተርአየ ጽጌ የተበረከተ

**ሚያዚያ 1 ቀን: 2006 ዓ.ም.**

**April 9, 2014**

የአቶ መላኩ አሰፋን የህይወት ታሪክ ለመግለጽ “ኀብረ ሐመልሚል ቀይህ ወጸዓድዒድ አርአያ ኮሰኮስ ዘብሩር”ብለን ውበት የምንገልጽበትን የግዕዝ ቋንቋ ሐረግ መነሻ ማድረጉ ተስማሚ ይመስለኛል። ይሁን እንጅ ያቶ መላኩን ሁለንተና ለመግለጽ ወደዚህ ውበት ገላጭ ሀረግ ከመግባቴ በፊት፤ በሩቅና በቅርብ ላሉት ዘመዶቹና ወዳጆቹ ህልፈቱን ለማርዳት ስለሚረዳ፤ ተወልዶ እትብቱ ከተቀበረባት መንደር ጀምሬ የረገጣቸውንና የቆየባቸውን ቦታወች ማስቀደሙ ተገቢ እንደሆነ እገምታለሁ።

አቶ መላኩ አሰፋ በወሎ ክፍለ ሀገር በቦረና አውርጃ ሌንጬ ማርያም በምትባለው ድብር ተወለደ። ከተወለደ በኋላ አባትና እናቱ ከአያቶቹ ጋር እንዲቆይ አድርገው ወደ ደቡብ መጥተው ስለነበረ በደብሩ ፊደልና ንባብ ያስተምሩ በነበሩት መምህር ፊደልና ንባብ እየተማረ አደገ። እድሜው ሲደርስ አባትን ናቱ ወደሚኖሩበት ሲዳሞ ክፍለ ሀገር መጣ። ያንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ይርጋ ዓለም ተከታተለ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአዋሳ ታቦር ትምህርት ቤት አጠናቀቀ። አዲስ አበባ በሚገኘው ሰንጋ ተራ በሚባለው ሰፈር ውስጥ በነበረው ጋራጅ የመካኒክ ትምህርት ተማረ። ባዋሳ እርሻ ጣቢያ የጎተራ ጥገና

ክፍል ሀላፊ ሆኖ  አገለገለ።

የቀዳማዊ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት የተካው ለውጥ ሲመጣ፤ በወቅቱ የነበረውን ስርአት ተቀብሎ አገሩን በሰፊው ለማገልገል በወሰደው ምርጫ በተለያዩ ህዝባውያን ያገልግሎት ዘርፎች ተሰማራ። የአዋሳ  ከተማ ምክትል ሹም ሆኖ  አገለገለ። አሁን ያለው መንግስት አገሪቱን ሲቆጣጠር ተሰዶ ኬንያ ናይሮቢ ገባ። ከናይሮቢ እህቱ ወደሚኖሩበት ወደ አሜሪካ  መጥቶ በዋሽንግተን ስያትል አሜሪካዊ ኑሮውን ጀመረ።  እህቱ  ከስያትል ወደ ሴንትሉስ  ሲመጡ ከሁለት ጓደኞቹ  ከአቶ ይሄነው ማዘንጊያና  ቀደም ብለው በሞት ከተለዩት ከአቶ ቀነኔ ኪቲላ ጋራ ወደ ሴንት ሉስ መጣ።



*አቶ መላኩ አሰፋና ባለቤቱ ወ/ሮ ወርቅነሽ ደስታ*

ባላቤቱ ወይዘሮ ወርቅነሽ  ደስታ ከስድስት ልጆቻቸው ጋራ ከኢትዮጵያ ወደ ሴንትሉስ  መጥተው በሞት እስከ ተለየ መጋቢት ፳፪ ቀን ፪ሺ ፮ ዓመተ ምህረት ድረስ ልጆቻቸውን እያስተማሩ አብረው ኖሩ። መላኩ ሴንትሉስ በቆየባቸው ዓመታት  በማህበራዊ ኑሮው ለህብረትሰቡ የሰጠውን አገልግሎት ህብረተ ሰቡን በመወከል ሁለት የህብረተ ሰቡ መሪዎች አቶ ገድሉ መታፈሪያና አቶ ነጋሲ ታፈረ  ገልጸውታል። አቶ ገድሉ መታፈሪያ፤  ፌሬዋን በወቅቱም ያለወቅቱም የምትሰጥ  ቅጠሏም የማይረግፍ፤ በተለያዩ ቀለማትና ድምጽ ተውበው ለተፈጠሩ አዕዋፍ ከተማ በሆነችው ዛፍ መስለው  የአቶ መላኩን ሕይወት ገልጸውታል። አቶ ነጋሲ ታፈረም "አንድነታችን በተፈተነበት ወቅት ሁሉ አቶ መላኩ ላንድነታችን መድፌና ክራችን ነበር" ብለው ገልጸውታል።  ለመላኩ በሴንትሉስ የተባለለትን ለሴንት ሉስ  ህዝብ ልተወውና፤ እንደ ጓደኛም እንደ ወንድምም  እንነጋገርባቸው የነበሩትንና  የተገነዘብኩትን ለመመስከር፤  የተወለደባትን እትብቱ የተቀበረባትን ሌንጮ የምትባለውን መንደር መነሻ አድርጌ ምስክርነቴን ባቀርበው የመላኩን ሁለንተና ይገልጸዋል ብየ አምናለሁ።

# ሌንጮ

ሌንጮ ምን ማለት እንደሆነ ባልረዳውም፤ የኦረሞኛ ቃል እንደሆነ እገምታለሁ። "በስመ ሀዳሪ ይጼዋ ማህደር። ወበስመ ማህደር ይጼዋዕ ሀዳሪ"  ቦታ በኑዋሪው ሰው ስም ይጠራል፤  ኗሪው ሰውም በቦታው ስም ይጠራል" እንደተባለው፤  በወሎ ክፍለ ሀገር ያለችውን ሌንጮ የምትባለውን  መንደር የቆረቆረ  ሌንጮ የሚባል ሰው እንደሆነ የሚያጠራጥር አይደለም። ሌንጮ ወደዚያች ቦታ እንዴትና

ለምን ሄደ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ ተገቢ ነውና፤ መልሱን የምናገኘው "ለይኩን" ብሎ ክርስቶስ ከተናገረው ቃለ መለኮት እና፤ ኅብረ ሐመልሚልነታችንን ከሚገልጸው ከታሪካችን ነው።

ክርስቶስ በቃለ መለኮቱ "አንተ በኔ፤ እኔ ባንተ አንድ እንደሆን። እነዚህም አንድ ይሁኑ" (ዮሐ ፲፯፡ ፳፩—፳፪)። ብሎ አዘዘ። በቃለ ትስብእቱ ደግሞ "አንድ ይሁኑ" ብሎ ጸለየ። "ይሁኑ" የምትለው ቃል፤ ትእዛዝንና ጸሎትን ያዋሀደች ቃል ናት። ይህችን ትእዛዝ መላኩም እኛም ሳናውቅ በዘመቻ፤ እያወቅን በጋብቻ ፈጽመናታል። ወደ ታሪካችን መለስ ብለን ከአክሱም ጀምረን መቃኘት ስንጀምር የፈጸምናትን አንድ የመሆን ትእዛዝ የበለጠ እንገነዘባለን ብየ እገምታለሁ።

# ከአክሱም እንጀምር።

ያንድነታችንን ሁኔታ ስንመረምር ሊቃውንት የተናገሩትን መነሻ ማድረጉ ተገቢ ይሆናል። ነቢዩ ኤርምያስ አለመቀየራችንን ለመግለጽ "ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዝጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? (ኤር፲፫፡፳፫)" ብሎ ከነብር ዝጉርጉርነት ጋራ እኛነታችንን ያወዳደረበትን ቃል፤ ሊቃውንት አባቶች "ኅብረ ሐመልሚል ቀይህ ወጸዓድዒድ አርአያ ኮሰኮስ ዘብሩር" በሚለው ውበት ገላጭ ሐረግ የኢትዮጵያዊነታችን ኅብረደም ግባት ያጎላምሱታል።

ይህም ማለት፡- "የአረንጓዴ ነጠብጣብ፤ የቀይ ነጠብጣብ፤ የነጭ ነጠብጣብ፤ የብዙ አይነት ቀለማት ህብር፤ በማይዝግ በብር ሰሌዳ ላይ በባለሙያ የተሰሩ የወርቅ፡ ያልማዝና የዕንቁ ፈርጦች እና ጉብጉባቶች" ማለት ነው። ይህም የኅብረ ደማችን ውጥንቅጥነት የኢትዮጵያዊታችን ውበት ነው። ይህ እንዴት በምን መንገድ ሆነ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ለዚህ ጥያቄ መልስ የምናገኘው የቃለ መለኮቱን መሠረታዊነት ሳንዘነጋ፤ ከላይ እንዳልኩት ከአኩስም ጀምረን ወደ ታሪካችን ዘልቀን ስንገባ ነው።

ከ8ኛው ክፍለ ዘመን በፊት አክሱም የሰው ዘር መናህሪያ ነበረች። ከጎረቤት አገሮች ከየመን ከግብጽ ከእስራኤል ከመካከለኛውና ከሩቅ ምስራቅ አገሮች ወደ አኩስም ከተማ ለንግድ፤ ከተማዋ ያፈራችውን ስልጣኔን ለመካፈልና በተለያዩ ምክንያቶች ብዙ የተለያዩ የሰው ዘሮች ይጣለፉባት ነበር። በዚያ ወቅት በዚህ ሁኔታ ከየአቅጣጫዎች የተሰበሰቡ ሁሉ ተዋልደዋል። ተቀላቅለዋል። ተቀይጠዋል። አንድ ሆነዋል። ይህ ሁኔታቸው "ኅብረ ሐመልሚል ቀይህ ወጸዓድዒድ አርአያ ኮሰኮስ ዘብሩር" የሚለው የውበት መግለጫ ሀረግ እንዲሰጣቸው አድርጓል።

በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ይህ የተቀየጠ ህዝብ የሚኖርባትን የአኩስምን ከተማ ዮዲት ስታፈርሳት፤ ከሞት የተረፈው ህዝብ ወደ መሀል ኢትዮጵያ ተሰደደ። ከዚያም ወደ ጠረፍ ወደ ባሌ አሩሲ ሀረር ድረስ ተበትኖ ካካባቢው ህዝብ ጋራ ተቀላቀለ። ተዋለደ በደም ባጥንት አንድ ሆነ። በ12ኛ ክፍለ ዘመን ከምሥራቅ ኢትዮጵያ የተነሳው ግራኝ መሀመድ በዮዲት ወረራ ምክንያት በመላ ኢትዮጵያ ተበትኖ በየደረሰበት በሀረር ባርሲ በባሌና በሲዳሞ ትዳር እየያዘ ንብረት እያፈራ ኑሮ የጀመረውን ህዝብ ሠራዊት አድርጎ ወደ መሀል ኢትዮጵያ በመዝመት እንደገና መለሰው። ይህም ማለት ወደ ቅድመ አያቱ ቦታ በዘመቻ መልክ ተመለሰ ማለት ነው።

ከሰሜን በዚህ ወቅት ባባቱ ወገብ ሆኖ በዮዲት ወረራ ወደ ደቡብ የተሰደደው ሌንጮ፤ እንደ ገና ካምስት ትውልድ በኋላ በዘመነ ግራኝ መሀመድ ማለት ነው፤ የግራኝ ሠራዊት ሆኖ ወደ ቅድመ አያቱ ወደ

መሀልና ወደ ሰሜኑ ከተበተነው ሠራዊት አንዱ በመሆን በደረሰበት በወሎ ክፍለ ሀገር ሌንጮ ብሎ በሰየማት ቦታ አረፈ። ትዳር መሰረተ። ንብረት አፈራ። ሌንጮ የሰፈረባትን ይህችን መንደር ሌንጮ ብሎ በስሙ ቆረቆራት። ይህች የመንደር ስም የመላኩን የሰውነት ድርና ማግ አርጋ ያፈራች "ኀብረ ሐመልሚል" ናት። መላኩ በዚህች ቦታ ተወለደ እትብቱም ተቀበረ።ውህና አፈር እየተራጨባት; ፊደል እየተማረበት የከብት እረኛም ሆኖባት አመታት ቆጠረባት። መላኩ ሌንጮ በተባለችው መንደር ቆሞ አልቀረም።

መላኩ ያባቶችን ባህል በመከተል፤ ሌንጮ ወደተወለደበት፤ የሌንጮ እትብት ወደ ተቀበረበት ወደ ደቡብ አገር ጉዞውን በተራው አቀና። ሌንጮ ወደ ተወለደበት ወደ ደቡብ አገር እንዲሄድ ለመላኩ ሌላ ምክንያት አለው። የአዋሳ ቅዱስ ገብርኤልን የመሰረቱት፤ በኋላም አሁን ባገልግሎት ላይ ያለው አዲሱ የአዋሳ ቅዱስ ገብርኤልን ተጀምሮ እስኪያልቅ የደከሙት አባቱን መምህሬ አሰፋ መኮንን በመከተል ጭምርም ነበር። [ሙሉ ታሪካቸውን ለማንበብ ከፈለጉ ይህን ይጫኑ]:: አባቱ መምሬ አሰፋም፤ መላኩ ከተወለደ በኋላ ከወሎ ወደ ደቡብ መጥተው ስለነበረ መላኩ ተከትሏቸው መጣ።

መምሬ አሰፋንስ ከወሎ ወደ ደቡብ ምን ወሰዳቸው? አካሄዳቸው ወፍ ዘራሽ ነበር? እሱንም እንመልከተው። መምሬ አሰፋ መኮንን ወደ ደቡብ የሳባቸው "ኀብረ ሐመልሚል" የሆነው ዘራቸው ነበር። የመምሬ አሰፋ ቅድመ አያት ዋቄ ይባል ነበር። ይህም የሚያሳየው ዋቄ የተባለው የመምሬ አሰፋ ቅድመ አያት ኦረሞ ነበር። መላኩ የተወለደባትን መንደር የቆረቆረው ሌንጮ ወደ ወሎ በሄደበት መንገድ፤ ዋቄም ወደ ወሎ ሄዶ፤ በወሎ ኑሮ ከጀመሩት ኦረሞዎች አንዱ ነበር ማለት ነው። ይህ የሚያሳየው መላኩ በሰውነቱ የተሸከመውን በአባቱ በኩል ያለውን የዘር ሐረግ ሲሆን፤ ካባቱ ሳንርቅ በሌላው ዘርፍ ስንመለከተው ገብረ ሥላሴ ምናሴ ገላውድዮስ የሚባሉ ሰዎች ተደርድረዋል። እነዚህም ከትግሬ፤ ከአማራ ከጉራጌና ከሌሎችም ዘሮች መሆናቸው ነው። ይህ የሚያሳየው መላኩ በናቱ በኩል ያለውን ሳይጨምር ባባቱ ብቻ የተሸከመው ሰውነት የትግሬው፤ ያማራው፤ የኦረሞውና የጉራጌው ሁሉ "ኀብረ ሐመልሚል" መሆኑን ነው። በዚህ ቦታ ዘሬ የሚቀበረው የመላኩ ሰውነት የዚህ የደም ግባት (ስብስብ) ወይም ጸአድዒድ ነው።

የመላኩን ሰውነት የሚገልጸው ሌላም ሳልጠቅሰው የማላልፈው ምሳሌ አለ። ይህም በቆሎ ትምህርት ቤት እየበላሁ የተማርኩበት የምግብ ዓይነት ነው። ኮፌዳችንን ይዘን በየመንደሩ ስንዞር የተለያዩ የእህል አይነቶች ከየቤቱ እንሰበሰባለን። ኬፌዳችን ለተለያዩ አይነቶች የተለያዩ ኪሶች የላትም። ኮፌዳችን ሁሉንም የምግብ አይነት ባንድ ላይ ቀላቅላ የምትይዝ ናት። ከየመንደሩ ለምነን የምናገኛቸው የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ወደ ኮፌዳችን ገብተው ሲቀላቀሉ ስማቸውን ይቀይራሉ። ውጥንቅጥ "ኀብረ ሐመልሚል" የሚል ያንድነት ስም ይሰጣቸዋል። መላኩ "ኀብረ ሐመልሚል ወይም አርአያ ኮሰኮስ ዘብሩር መሆኑን ያየነው በሰውነቱ ብቻ አይደለም። በማህበራዊ ባህርዩም በመሬት የነበረውን ስእቱን ስሜቱን የሚገልጽባቸው ብዙ ነገሮች ነበሩት።

አጼ ምንይልክ ተናገሩት እየተባለ የሚነገርላቸውን በምሳሌነት ብጠቅሰው ይገልጸዋል ብየ እገምታለሁ። አጼ ምንይልክ ኢትዮጵያን በሚሩበት ዘመን አንድ ኢትዮጵያዊ "የሥጋ ዘመዴ ነዎ ብየ ወደ አጼ ምንይልክ ብቀርብ ሹመት በማግኘት መከበር እችላለሁ" ብሎ አሰበ። "የሥጋ ዘመዴን ንጉሥ ምንይልክን ማግኘት እፈልጋለሁ" እያለ ወደ ቤተ መንግሥት መጣ። አጼ ምን ይልክ "ግባ በሉት" ብለውት ገባ። በእንግድነት ተቀበሉትና ተከብሮ ሰነበተ። ለመሄድ ሲሰናበት አንድ ብር ብቻ ሰጡት። "ምነው ምነው የሥጋ ዘመደዎን እንደ ባእድ በዚህች ብቻ ሸኙኝ" ብሎ ተናገረ። እሳቸውም "እንዴት ነበረ

ዝምድናችን? ብለው ጠየቁት። እሱም መለሰና “በአዳም  በኩል ነዋ” ብሎ መለሰላቸው። እሳቸውም፤ መለሱና “ዝምድናችን በአዳም በኩል ከሆነማ ያለኝን ለአዳም ዘር ሁሉ ባካፍል አሁን የሰጠሁህን  ያህል አይደርስህም” ብለው ሸኙት ይባላል። መላኩ ለቤተ ሰቡ ሳያዳላ ለሰፊው ማህበራዊ መረቡ ይበልጠውን ሰአት በመስጠቱ፤ ከቤተ ሰቡ ለሚቀርብለት ጥያቄ የሰጠኋችሁን ያህል አይደርሳችሁም” የሚል ነበር።

አቶ ነጋሲ ታፈረ “አቶ መላኩ ለችግራችን ሁሉ ጠጋኝ መድፌና ክራችን ነበር” እንዳሉት፤  ሰአቱን ሁሉ ያሳልፍ የነበረው የተጣላ ሲያስታርቅ፤ የተራራቁትን ሲያቀራርብ፤  ከውጭ የመጡትን እንግዶች አገር ሲያሳይ ሲያለማምድ፤ መጓጓዣ አጥተው የተቸገሩ ኢትዮጵያውያንን ሲረዳ  ነበር።  በዚህ ስሜቱ ያገለገለው ህዝብ በዚህ ከተማ ብቻ አልነበረም። በዓል በሚከበረበት ቦታ ሁሉ ለሚሄዱት  ሰዎች ስራውን ትቶ  ሹፌር እየሆነ  ያገለግል ነበር። የአገልግሎቱን ስፋት ይገታው የነበረው፤ ድካምና መሰልቸት ሳይሆን የጸሐይ ጥልቀ ነበር። በጥቅሉ “አንተ በኔ፤ እኔ ባንተ አንድ እንደሆን። እነዚህም አንድ ይሁኑ” (ዮሐ ፲፯፡ ፳፩—፳፪)። ብሎ ክርስቶስ ያዘዘውን መላኩ በሥጋውም በስሜቱም ፈጽሞታል።

የመላኩ ሰውነት   አርአያ ኮሰኮስ ዘብሩር የተባለውን  የሁላችንን ሰውነት  የምንመለከትበት መስተዋታችን ነው።   በሌላ  አገላለጽ “ኢትዮጵያዊነታችን በለመለመ መስክ በቅለው፤ አብበው፤  በሩቅ የሚታዩ  የጽጌ ረዳ፤ የአደይ አበባ፤ የሶሪት አበባ፤ የሱፍ አበባ መሳይ ይህ ቀረሽ የማይባል የውበት ውጥንቅጥ ማለት ነው። ከዚህ ውጭ ነኝ የሚል ኢትዮጵያዊ ካለ፤ ወፍ ዘራሽነትህን ተቀብለህ ቦታህን ፈልግ ሊባል ይገባዋል” እያሉ ሊቃውንት አበው አስተምረውናል።

የሰውነታችን ተፈጥሯዊ  አሰራራችን  ውጥንቅጥ ነው። ኢትዮጵያም ልንጠነቀቅላት የሚገባን የወጥንቅጥነታችን ኮፌዳችን ናት። ቤተ ክርስቲያናችንም የታሪካችን ማህደር ናት። “አርያ ኮሰኮስ ዘብሩር” ናት ማለትም “የወርቅ፤ ያልማዝና የዕንቁ ፈርጦች (ጉብጉባቶች” ን የተሸከመች የማትዝግ የብር ሰሌዳ ነት። ዛሬ በወንድማችን በመላኩ ሞት የሚናወጠው ሰውነታችን፤  በሀዘን የሚታመሰው ደማችን የኛነታችን ውጥንቅጥ ነው። የሚፈሰው እንባችንም  ከእኛነታችን የሚፈልቅ “ኅብረ ሐመልሚል” ነው።

መላኩ በሰውነቱ ቅንብር። በግብሩና  በባህርዩ  ያንጸባርቀው የነበረው ይህንኑ ነበር። መላኩ ለእኛም ለወለዳቸው ልጆቹም ትቶልን የሄደው የማይረሳ መታሰቢያው (ተዝካሩ)  ይህ የተረዳነውና የቃኘነው ሰውነታችን ነው። መላኩም ትንፋሹ እስክትቆም ድረስ እየተናገረ ብግብሩም እያረጋገጠ የዚህ ዓለም ሩጫውን  አቋረጠ። በተረፈ ከመላኩ አብራክ የፈለቁትን  አጽቆቹን (ልጆቹ)  ክርስቶስ “በብር ሰሌዳ የተቀረጹ የማይዝጉ የወርቅ ጉብጉባት” እንዲያደርጋቸው  እየተመኘን ከኛ  ለተለየበት ጉዘው በምናደርግለት አሸኛኘት ዛሬ መጋቢት ፳፫ ቀን ፪ሸ ፮ ዓ/ ም እንሰናበተዋለን።

“ወስብሀተ እግዚአብሔር ላዕሌሃ፤ ወከዋክብቲሃኒ ይመስሉ  ከመ ዕንቁ ክቡር ወጽዕዱት ይእቲ ከመ አስሐትያ ራዕይ ፳፩፡፲፩—፲፪)” በእግዚአብሔር ክብር ከምታበራው፤ የብርሃኗ ድምቀት እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ እንደ ኢያሴጲድ እንደ መስተዋት የጠራ ነው” ከተባለችው፤ ውበቷንና ድምቀቷ ቋንቋችን ከሚገልጻት “ኅብረ ሐመልሚል” በላይ ከሆነችው፤ ጻድቃን ሰማእታት ካሉባት፤ ታቦት ዘዶር ቅድስት ድንግል ማርያም ካለችበት፤ ራሱ ንጉሣችን ክርስቶስ በነገሠባት በሰማያዊቷ በጽዮን ከታማ  ሁላችንንም ከመላኩ ጋራ  ያገናኝን።